# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲዎሪ መጽሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተዘጋጀ

ሰኔ 1962

# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲዎሪ መጽሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተዘጋጀ

አዘጋጅ፦ ንጉደ ጉዘዜ

ዋጋው አንድ ብር

ሐሌ 1962

## ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ እንደራጅ

« . . . ለብዙ አመታት ታዛቢዎች ከንጉሰ ነገስቱ በኋላ በ ኢትዮጵያ ላይ የገሃነም እሳት ይወርዳል ሲሉ ነበር።አሁን ግን እንደዚ ህ አይነቱ መአት ንጉሰ ነገስቱ እስኪያልፍም የሚጠብቅ አይመስልም የኢትዮጵያ እልቂት ከኮንጎ፣ከቢያፍራና ከሱዳን ይበልጥ አሰቃቂ ይሆ ናል።በኢትዮጵያ ውስጥ እስላሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ጨካኝ ጦረኞ ች ናቸው።ይህ በዘመናዊ መሳርያ የሚያደርጉት ሪቮሉሽን ወይም ደግ ሞ የእርስ በእርስ ፍጅት አስደናቂውን "የኢትዮጵያ ታሪክ" ከፍፃሜ ያ ደርሰዋል »(1)

እንደዚህ አይነቱ አነጋገር፣ታዛቢ ነኝ የሚል ሁሉ ስለኢት ዮጵያ የሚያቀርበውን ፅሁፍ የሚደመድምበት አቡነዘበሰማያት ሆኗል ስለኢትዮጵያ ዕድ ከሀይለስላሴ በኋላ ታሪኳ ይደመሰሳል፣ኢትዮጵያ ት ጠፋለች፣ህዝብዋ ይተላለቃል በማለት የሽብር ቃሉን ሳይሰነዝር ብእሩን የሚያስቀምጥ ታዛቢ እየጠፋ ሄዷል።

እርግጥ መጪው ጊዜ ታላቅ የለውጥና የትርምስ አውሎ ነፋስ ያዘለ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።በታሪካችን እንደምናየ ው የበዝባዦች "በውርስ ዘመን" ጊዜ መተረማመስ የተለመደ ነው።ዛሬ ግን ይህንም የሚያባብሱና ልዩ መልክ የሚሰጡ ልዩ አዳዲስ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።የኢትዮጵያ ህዝብ እያደር እየጠነከረ በሚሄደው ጭቆና በመመረር በያለበት በበለጠ በመነሳሳት ላይ ነው።የባእድ ሃይሎች ጣል ቃ ገብነት ከመቸውም ይበልጥ በሀገራችን ስር ሰዶ ሀገራችንን ጥገኛ ስ ላደረጋት አገር ወዳድ ሁሉ ማጉረምረም ጀምሯል።

ለዚህ ለማይቀረው ተጋድሎ ሁሉም እንደመሰለው በመ ደራጀት ላይ ነው።ገዢዎቻችን በዘረፋው ድርሻ አለመስማማት ለሚመ ጣው ጭቅጭቅም ሆነ ወይም በፀረ ህዝብ አንድነታቸው ለመደላደል ውስጥ ውስጡን በመደራጀት ላይ ናቸው።የኢትዮጵያ ህዝብ በዝባዦ ቹ እንደዚህ ከዘረጉለት ወጥመድ ውስጥ ከገባ እውነትም አሰቃቂና ከ

(1) ቁጥር ለተደረገባቸው ሁሉ በፅሁፉ መጨረሻ ማብራሪያ ይሰጣል

ንት፡ ደም መፋሰስ ይመጣል።የኛ አላማ ይህ የማይቀር ትንንቅ መስመር
ይያዝ የሚል ነው፡እንደሚይዝም ሙሉ ተስፋ አለን።ተበዝባዝ በበዝ
ባዥ ላይ እጁን እንዲያነሳ፡ለነፃነት ትግላችን ሊውል የሚገባው ሀይል
በከንቱ ትርምስ የትም ባክኖ እንዳይቀርና የነፃነት ትግላችን ከሚገባው
በላይ እንዳይራዘም የሚያስፈልገው ከአሁኑ የተበዝባዡ ህዝብ በሙሉ
በአንድ ግልፅ በሆነ ፕሮግራምና የስራ ውጥን አማካኝነት መደራጀት ነ
ው።ለዚህም ሰላምን፡ነፃነትን፡እርምጃንና አገሩን ወዳድ የሆነ ኢትዮጵያ
ዊ ሁሉ የማይቆጠብ ጥረቱን ማበርከት አለበት።

መጭውን ጊዜ ታላቅ የትግል ማእበል ያዘለ የሚያደርገው
ምንድነው? ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም፡ነፃነት፡እርምጃና ብልፅግና የምንቆ
ረቆር ኢትዮጵያዊያን ተግባራችን ምንድን ነው? እነዚህን ጥያቄዎች በ
መጠኑ ለመመለስ እንሞክራለን።ሀሳባችን በዚህ ታላቅ ጉዳይ ላይ መሰ
ረታዊ የሆኑ አንዳንድ አስተያየቶች ለመሰንዘርና ውይይት ለመክፈት
እንጂ ለእንደዚህ አይነቱ ሰፊ ጉዳይ የተሙዋላ መልስ ለመስጠት አይ
ደለም።

I

መጪው ጊዜ የትግልና የትርምስ መሆኑን ለመረዳት ያለ
ፈውን ታሪካችንን፡የዛሬውን የሃገራችንና የአለምን ሁኔታ መመልከት
ያስፈልጋል።

በታሪካችን "የውርስ ጊዜ" የስልጣን ትግልና ታላላቆች ብ
ላባቶች ለጥቅም ሽሚያቸው ሲሉ ህዝቡን በዚህ ቅደም በዚያ ተሰለፍ እ
ያሉ የሚያፋጁበት የትርምስ ወቅት ነው።ሪቻርድ ግሪንፊልድ በዚህ ጉ
ዳይ ሲፅፍ «የኢትዮጵያ ታሪክ በግልፅ እንደሚያሳየን ዘውድን ለመቀ
ዳጀት ከንጉስ መወለድ ብቻ፡ምንጊዜም በቂ ሆኖ አያውቅም።እስከዛሬም
ቢሆን ሀይለኛ ባላባቶች (እንደልማድ አድርገውት) በውርሱ ላይ ለማ
ደምና ስልጣን ለመሻማት አመንትተው አያውቁም» (2) በማለት አት
ቷል።

ያለፉትን የመቶ አመታት ታሪካችንን ዘወር ብሎ ማየት ብቻ
ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው።የቴዎድሮስ ሞት ከስከተለው ትርምስ በኋላ የ
ጊዜው ባለሀይል ዋግሹም ጉበዜ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ዙፋኑን



ይዘው ነበር።ይበልጥ የደረጀ ሃይል ያጠራቀሙት ደጃች ካሳ በሶስት አ
መት ውስጥ ተክለ ጊዮርጊስን ከአልጋ አውርደው አፄ ዮሀንስ ተባሉ።
አፄ ዮሀንስ መተማ ሲወድቁ ዙፋኑን ለልጃቸው ለራስ መንገሻ "ቢናዘዙ
ም" የንጉሰ ነገስቱ ዘውድ ለጊዜው ባለሀይል፡ለሸዋው ምኒልክ ሄደ።ከአ
ፄ ምኒልክ በኋላ የልጅ እያሱን፡የኢቴጌ ጣይቱንና የራስ ተፈሪን የስል
ጣን ትንንቅና ያስከተለውን ትርምስ ሁላችንም የምናውቀው ነው።ይህ
ን ሁሉ ማለታችን አጥንት ቆጠራውን እስከዚህም ዋጋ ሰጥተነው አይደ
ለም።ታሪክን በሬ ወለደ እያሰኙ ዘውድ የሰላምና የአንድነታችን ዋስት
ና ነው ለሚሉ ሁሉ፡እንዲያውም "የውርስ ጊዜ" የትግል፡የፍጅትና የት
ርምስ ወቅት መሆኑን ለማስታወስና አሁንም ጨቋኞች እንደለመዱት
ለጥቅም ሲታገሉ ህዝባችንን እርስ በእርሱ እንዳያፋጁት ከታሪክ እን
ማር ለማለት ነው።

ከዚህም በላይ "መጪው ጊዜ የትግል ማእበል አዝሏል" ለ
ማለት የሚያስችለን ምርኩዛችን የጊዜው የኢትዮጵያና የአለም ሁኔታ
ነው።ዛሬ በኢትዮጵያ ሁለት ጉልህ ነገሮች እናያለን።መጀመሪያ ነገር በ
ህዝቡና በታላላቅ ባላባት መካከል ያለው ጠብ እየከረረ ሄዷል።ስለዚህ
ም በአለፉት አመታት በያለበት የተጀመሩት ትግሎች እየተፋፋሙ ሄ
ደዋል።ሁለተኛ ደግሞ በአገራችን ጉዳይ ከመቸውም ይበልጥ ኢምፔሪ
ያሊስቶች ጣልቃ ሲገቡ እናያለን።የኢምፔሪያሊስቶችን ጉዳይ በሃገራ
ችን ወስነን ልናየው አንችልም።በአፍሪቃ፡በእስያና በላቲን አሜሪካ ፀረ
ኢምፔሪያሊስት ህዝቦች ተነስተው በመታገል ላይ ናቸው።ይህ በኢም
ፔሪያሊዝምና በአለም ተበዝባዥ ህዝቦች መካከል የሚደገረው ትግል
ለዘመኑ መልክ ከሚሰጡት ገድሎች ዋናው ነው ብለን እናምናለን።መ
ጪው ጊዜም በአለም (በሃገራችንም) ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆነው ት
ግል እየበረታ የሚሄድበት መሆኑን መረዳት አዳጋች ነገር አይደለም።

በባላባቶቹ መንግስትና በህዝብ መካከል ያለው ጠብና መቆ
ራረጥ እየከረረ ሄዷል።በየጊዜው እንደምናያቸው የባላባቶቹ መንግስ
ት እንኳን ተገቢ የሆኑትን የህዝብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማርካትና
ቆሞ ለመሄድ እንኳን ህዝቡን በይበልጥ ለመዝረፍና ለመጨቆን ተገዷ
ል።ይህም ስርአት እስከተሻረ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ እድል እርምጃና

ብልፅግና ሳይሆን ይበልጥ መራቆትና መጨቆን መሆኑን በፍፁም አንጠራጠርም።ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ የባላባቶቹን ጭቆና ለመቋቋም ይነሳል።ተነስቷልም።ይህን ስንል በከንቱ ምኞት ላይ በተመሰረተ ቅዠት ተመርተን አይደለም።የኢትዮጵያ ህዝብ የባላባቶቹንና የኢምፔሪያሊስቶችን ዘረፋ ተቋቁሞ የደህንነቱን መንገድ በትግሉ ለመትለም የሚነሳው እየተባባሰ የሚሄደው ጭቆና ስለሚያስመርረውና ሌላ ምርጫ በመንሳት ለቆራጥ ትግል ስለሚገፋፋው ነው።ነገር ግን በጭቆና ተመርሮ መነሳት ብቻ የእውነተኛ ነፃነት ዋስትና ሊሆን አይችልም።በሌላው አፍሪቃና ሩቅም ሳንሄድ በገዛ ሃገራችን እንደምናየው የህዝቡን ሀይል ለማባከን፣አንድነቱን ለመስበርና ጥቅማቸውን ለመጠበቅም ሆነ ለማደርጀት በዝባገሮች ህዝቡን በነገድና በሀይማኖት እያለያዩ ሊያፋጁት ይችላሉ።ለዚህም የተከማቸው የህዝብ ቁጣና ሀይል ለዋናው የነፃነት ትግል ሳይውል ለብዙ ጊዜ በነገድና በሀይማኖት ትርምስ የትም ባክኖ እንዳይቀር መጠንቀቅም ያስፈልጋል።

ሁለተኛ ደግሞ የጊዜው የአለም ሁኔታ አለ።ኢትዮጵያችን እንደቀድሞው "በራሳቸው አለም ተረስታ" አልተኛችም።በተለይ ያለፉት መቶ አመታት ታሪካችን ደግሞ እንዳሳየን በሃገሪቱ ውስጥ የሚደረገው የስልጣንና የጥቅም ትግል የውጭ ዘራፊዎችም እንደየጥቅማቸው ጣልቃ እየገቡ የሚፈተፍቱበት ግርግር ነው።አፄ ዮሃንስ ዙፋኑን ለመያዝ የተገለገሉበትን ብዙ መሳርያ ለማከማቸት የቻሉት በአፄ ቴዎድሮስ ላይ በተደረገው ዘመቻ ከእንግሊዞች ጋር በመተባበራቸው ነበር።አፄ ምኒልክ ዘውዱን ለመቀዳጀት ከኢጣልያኖች ብዙ የገንዘብና የመሳሪያ እርዳታ ማግኘታቸውን ታሪክ ይመሰክራል።በልጅ እያሱና በራስ ተፈሪ መካከል ትንንቁ ሲካሄድ ፈረንሳይ፣እንግሊዝና ጣልያን ራስ ተፈሪን ሲያግዙ ጀርመንና ቱርክ ደግሞ ወደልጅ እያሱ ያዘነበሉ እንደነበረ ይታወሳል።አፄ ምኒልክ አርጅተው የውርሳቸው "ጣጣ" የጊዜውን ኢምፔሪያሊስቶች በጣም አስግቷቸው በነበረ ጊዜ የኤሪትራ ገዠ የነበረው ሲኞር ማርቲኒ የኢምፔሪያሊስቶችን ጣልቃ ገብነት ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏል።«በኢትዮጵያ መጭው ጊዜ በጣም አጠራጣሪ በመሆኑና አፄ ምኒልክም እያረጁ በመሄዳቸው ታላቋ ብሪታኒያ፣ኢጣልያንና ፈረንሳይ በአንድ



ነት ሆነው ከቀረቡት ወራሾች ሁሉ የትኛውን እንደሚደግፉና ከስፈለገም የትኛውን የግድ እንደሚያነግሱ ከአሁኑ መስማማት ይገባቸዋል።በዚህ ጉዳይ ምንም አይነት ክርክርም ሆነ የሃሳብ ልዩነት ሊኖር አይገባም»።(3) ይህ የተነገረው የዛሬ ሃምሳ አመት ነው!

ከዛሬ ሃምሳ አመት ይልቅ ዛሬ በሀገራችን ኢምፔሪያሊስቶች ይበልጥ እጃቸውን ያስገቡ መሆናቸውን ለማስረዳት ብዙ መዘብዘብ አያስፈልገንም።ዛሬ በሀገራችን የገነነው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የመከላከያ ሀይላችንን፣ትምህርታችንን፣የኢኮኖሚያችንን ቁልፎች በእጁ ጨብጦ እንደያዘ ሁሉ ያውቃል።ነገ ከላይ ከሚፋጩት ሀይሎች ለጊዜው ገናና የሚሆነው የአሜሪካኖችን ድጋፍ የሚያገኘው አድሃሪ ሀይል መሆኑ አይከድም።ለዚህም የሚደረገው ዝግጅት የአደባባይ ምስጢር ሆኗል።በቅርቡ ሮጀርስ የተባለው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ወቅት "ለ ሞንድ" የተባለው ጋዜጣ ሲፅፍ እንዲህ ብሏል።«አፍሪቃን በሚዞርበት ጊዜ ሚስተር ሮጀርስ ዋሽንግተንን በሚያሳስቡ ሁለት ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ይችላል።ይኸውም እያረጁ የሄዱት የሀይለስላሴና የጆሞ ኬንያታ ውርስ ጉዳይ ነው . . . በተለይ የኢትዮጵያ ጉዳይ የአሜሪካን መሪዎች በጣም የሚያሳስባቸው ነው . . .»(4)

ከዚህ በፊት እንደተባለው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ጥቅማቸውን የሚጠብቅላቸው ከሆነ ወልደ ጊዮርጊስን ሆነ ወልደ ገብርኤልን ቢደግፉ ግድ የላቸውም።ነገር ግን አሜሪካኖች ስለደገፉት ብቻ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተወዝፎ ብዝበዛውን የሚቀጥል መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖር አይችልም።ከግማሽ ሚልዮን በላይ የሚሆኑ የአሜሪካና የጥገኞቹ ወታደሮች ዘምተውበት በጀግንነት የተቋቋማቸው የቬትናም ህዝብ ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው።ለኢትዮጵያ ህዝብ ከውጭ የመጣን ጠላት መቋቋም ደግሞ ሩቅ ሳንሄድ የጣልያን ዘመን አርበኝነቱ በቂ ምስክር ይሆናል።ስለዚህ የአሜሪካኖችን ድጋፍ ያገኘ ሁሉ በፈላጭ ቆራጭነት ይገዛል ማለት ከንቱ ምኞት ነው።

በዚሁ አያይዘን ጠቅላላውን የአለም ሁኔታ የተመለከትን እንደሆን የህዝቦች ሁሉ ጠላት የሆነው ኢምፔሪሊዝም በያለበት እየተወጠረ ሲያዝ እናያለን።በእስያ በተለይም በኢንዶቻይና ህዝቦች ፀረኢም

ፔሪያሊስት አንድነታቸውን አጠንክረው ትግላቸውን በመምራት ላይ ና
ቸው።የላቲን አሜሪካ ህዝቦች የያንኪዎችንና የአሽንጉሊቶቻቸውን ብ
ዝበዛ ለመቋቋም በያለበት ለትግል ተሰማርተው ይታያሉ።በአፍሪቃም በ
አንጐላ፣በጊኔ (ቢሳው)፣በሞዛምቢክ፣በደቡብ አፍሪቃና በዚምባብዌ የህ
ዝቦች የነፃነት ትግል እየተፋፋመ ሄዷል።በመካከለኛው ምስራቅ ከሃያ
አመታት በፊት ቤትና ንብረቱን ለቅቆ የተሰደደው የፍልስጤም ህዝብ
ከፅዮናዊያን፣ከኢምፔሪያሊስት ጠባቂዎቻቸውና ከአረብ አድሃሪዎች ጋ
ራ የሚደርገው ትግል እንደ ሰደድ እሳት ቀበሌውን በማዳረስ ላይ ነው
በያለበት የተበዝባጋር ህዝቦች ትግል እየደረጀ ሄዷል።የዚህ አለም–አ
ቀፍ ትግል አውሎ ንፋስ በኢትዮጵያችንም ላይ መንፈሱ ምንም ጥርጥ
ር የለውም።ኢምፔሪያሊዝም ተደምስሶ ህዝቦች ነፃ እስኪወጡ ድረስ ት
ግሉ እየተፋፋመ የሚሄድ መሆኑ ግልፅ ነው።

ባጭሩ ከዚህ በላይ እንደዘረዘርነው መጭው ጊዜ በየምክን
ያቱ የተጠራቀመ የትግል ማእበል ያዘለ መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል።
የዚህ አውሎ ንፋስ ዋና መነሻ አድርገን የምንቆጥረው የጊዜውን የሀገ
ሪቱን የኢኮኖሚ፣የሶሻልና የፖለቲካ ሁኔታ ነው።በዝባዦቹ የሚያደር
ጉትም ፀረህዝብ መፍጨርጨር የወሰደውን መልክ ቢወስድ ዞሮ ዞሮ አ
ላማው የህዝባችን መበዝበዝ እንዲቀጥል፣አንድነቱ ጠፍቶ እንዲደክም
ዘልአለማዊ የሚመስላቸው ስርአታቸው እንዳይናጋ መሆኑን እናውቃ
ለን።

ታድያስ ኢትዮጵያን ለማዳን? ነፃነታችንን ለመጐናፀፍ ?
ወደፊት ለመራመድ? እኛ ለዚህ ከአንድ መንገድ ሌላ ምንም አይታየ
ንም።የኢትዮጵያ ተበዝባጋር ህዝብ እውነተኛ ጠላቶቹን ከኢትዮጵያ መ
ሬት ለማጥፋት ባንድነት ተደራጅቶ መታገል አለበት።የኢትዮጵያ ህዝ
ብ ጠላቶቹን ወደጐን እየተወ እርስ በእርሱ እንዲፋጅ አንፈልግም።የ
ኢትዮጵያ ህዝብ ከዘመን ዘመን የላቡን ፍሬ መገበሩ አንሶት ለጥቂት ስ
ግብግቦች ጥቅም ማዳበሪያ ደሙ እንዲፈስ፣ወንድማማች ልጆች በከንቱ
እንዲተላለቁ አንፈልግም።ነገር ግን አውሎ ንፋሱን ገምተን ከአሁኑ ል
ንቋቋመው ካልተደራጀን ነገ በሚደረው ትንንቅ ህዝባችንን በዝባዦች
ሲያወናብዱት፣ከግራና ከቀኝ ኢምፔሪያሊስቶች ግራ ሲያጋቡት ሁሉም



በጠባብ መንደሩ፣በጠባብ ነገዱ፣በጠባብ ሃይማኖቱ ተውተብትቦ የሰፊው
ን የኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ አንድነት ዋናውን የድሀና የሀብታም
ትንንቅና እውነኛውን የነፃነት ትግል ማሰብ ይቸግራል።ዝለዚህም በመ
ሰረቱ ፀረባላባትና ፀረኢምፔሪያሊስት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግ
ል ሊዘበራረቅና ለጊዜው የተፈለገውን ውጤት ላያስገኝ ይችላል።

የኢትምጵያ ህዝብ ጭቆናን ለመቋቋም በያለበት በመነሳሳ
ት ላይ ነው።የህዝባችን ትግል በያለበት ከተደራጀ ትግሉ የሚያስከትለ
ውን መከራ ለመቀነስም ሆነ የሚያስገኘውን ፍሬ ዋጋ ያለው ለማድረግ
ይቻላል።ስለዚህም ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ እውነተኛ ሰላም፣አንድነት፣ነ
ፃነትና እርምጃ የሚቀረቁር ሁሉ ፀረባላባትና ፀረኢምፔሪያሊስት አላማ
ላይ ተመስርቶ የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ ባአንድ ግንባር የሚያሰልፍ
የትግል ድርጅት እንዲቋቋም መጣር አለበት።

ለመሰረታዊ ለውጥ እንቅፋት የሆኑትን ፀረህዝብ ሀይሎች
ህዝቡ በሙሉ በአንድነት ተደራጅቶ ሊታገላቸውና ሊደመስሳቸው ይገ
ባል።ለዚህም ዛሬ የገገርው ቡድን በሚያደርገው ምስጢራዊ ዘረፋና የ
ውርስ ዝግጅት አንፃር ህዝቡ በግልፅ ለለውጥና ብዝበዛን ጨርሶ ለግጥ
ፋት የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት።ለዚህም ከሁሉ
አስቀድሞ በህዝቡ መሰረታዊ ፍላጐቶች ላይ የተመሰረተ ግልፅ የስራ
ፕሮግራም ያስፈልጋል።የዚህ ፕሮግራም ዋና ዋና መልኮቹ ከዚህ በፊት
በተማሪዎች ጉባኤዎች ተደጋግመው ተገልፀዋል።

ዋናው አላማ የጢሰኛ ገበሬና የላብ አደሩን ጥቅም ለመጠ
በቅና ለማደራጀት ነው።ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሊወሰን አይገባም።አይች
ልምም።ሌሎችም በባላባቶችና በኢምፔሪያሊስቶች ዘረፋ የተመረሩ አ
ገር ወዳድና የህዝብ ወገኖች ሞልተዋል።ስለዚህ ይህ ፕሮግራም የነዚህ
ንም የህዝብ ወገኖች ጥቅም የሚጠብቅ ሰፊ የስራ ውጥን መሆን አለበት

–II–

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ከተውተበተበበት አዘቅት ወጥቶ አ
ዲስ ህይወት ይጠይቃል።መብቱም ነው።በሃብታምና በለምለም ሃገር ው
ስጥ ላቡን አንጠፍጥፎ የሚኖር ህዝብ ከድህነት፣ከርሃብና ከድንቁርና ጨ
ርሶ የተፋታና በደንብ የተሟላ ኑሮ ሊኖር ይገባዋል።የሀገራችን ህዝ

ብ በሙሉ ከህፃን እስከ ሽማግሌ ጤናው በደንብ ሊጠበቅ ይገባል።የሃገ
ራችን ወጣቶች በሙሉ የትምህርት ብርሃን ማግኘት አለባቸው።በቂ ጉ
ልበትና ትምህርት ያለው በሙሉ ሰርቶ ራሱን ለመቻል መብት አለው።
ባለውለታው አርበኛ፣ጡረ ያጣው ላብ አደር፣ሰብሳቢ ያጡት ህፃናት ሁ
ሉ ከሚገኙበት የሰቀቀን ኑሮ ተላቀው፣በሃገራቸው ያጡትን እምነት፣በ
ሰውነታቸው ያጡትን ኩራት መልሰው መጐናፀፍ አለባቸው።ህዝቡ በ
ሙሉ ንፁህ ውሃ ያስፈልገዋል።የመብራት ሀይል ያስፈልገዋል።ቁሳቁሳ
ዊ (material) ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ፍላጐቱን የሚያረካባቸው የመ
ዝናኛ ድርጅቶች ያስፈልጉታል።ለዚህም በቂና የተወሰነ የእረፍት ጊዜ
ያስፈልገዋል።ይህ ነው የምንመኘው ኑሮ።ይህ ነው የሚጨበጥ ነፃነት።
የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህን መሰረታዊ ፍላጐቱን ለማርካት
ተደራጅቶ መታገል አለበት፤ይታገላልም።የበዝባዦቹ የፕሮፓጋንዳ ጋጋ
ታ እስከአጥንቱ ስርስር የገባውን ድህነት፣መራቆትና ቅጥ ያጣ የኑሮ ፈ
ትና ሊያስረሳው አይችልም።እነዚህንም ፍላጐቶች ለማርካት ፈጣንና ት
ልቅ የኢኮኖሚ እድገት ያስፈልጋል።በያለበት ፋብሪካ ማቆም፣ግድብ መ
ገንባት፣መስና መንገድ፣በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም፣የእርሻን ዘዴ ማ
ሻሻል፣በጭሩ የሃገራችን ይህ ነው የማይባሉና የተሰበጣጠሩ የተፈጥሮ
ና ሰብአዊ ሃብቶች ለመላው ህዝብ ጥቅም ስራ ላይ መዋል አለባቸው።
እነዚህ ፍላጐቶች ሰፊና ጥልቅ በመሆናቸው በቀላሉ ሊከና
ወኑ አይችሉም።የመላ ህዝቡ ፍላጐቶች ስለሆኑ በጠቅላላው የህዝቡን
የተደራጀና ሆን ብሎ የተነሳ ጥረት ይጠይቃሉ።ሃገራችን ሀብታም ነች።
ህዝባችን ታታሪ ነው።ኑሮው በይሙዋላ ህዝቡ በሙሉ ታጥቆ የሚበክ
ነው ለጥቂት በዝባዦች መትረፍረፍ በመሆኑ ነው።ስለዚህም ይህ ጥቂ
ቶች በጥቅም ተሳስረው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጫኑት የብዝበዛ ስርአ
ት ተሰባብሮ መውደቅ አለበት።በሱም መቃብር ላይ እነዚህን የህዝብ ፍ
ላጐቶች ለማርካት ህዝቡ ተደራጅቶ የሚሰራበትና ጥቅሙን የሚያዳብ
ርበት፣ወደፊትም የሚራመድበት አዲስ ህዝባዊ ስርአት ያስፈልጋል።
ከምንታርጋቸ ጉባኤያችን ወዲህ ለዚህ ሁሉ በኢትዮጵያ
"ህዝባዊ መንግስት" አስፈላጊ መሆኑን አስረድተናል።ለዚህም ህዝባዊ
መንግስት የተደራጀ ህዝባዊ ትግል ያስፈልጋል።የሚደራጀው ማነው?



ይህን ለመረዳት ትግሉ ከማን ጋር እንደሆነና የትግሉስ ውጤት ማንን
እንደሚጠቅም መመልከት ያስፈልጋል።
የዛሬው የንጉስ ነገስት መንግስት የንጉሰ ነገስቱን፣የታላላቅ
ባላባቶችን፣የታላላቅ ካህናትን፣የከፍተኛ ሹማምንትን፣የባእድ በዝባዥ
ችን ጥቅም ለመጠበቅ የቆመ፣የዘራፊዎች "ወኪል ድርጅት" ነው።እኛ ደ
ግሞ የህዝብ መንግስት የምንለው ዛሬ ተደራጅተው የሚጨቁኑትን ዘ
ራፊዎች በሙሉ አስወግዶ የህዝብን ጥቅም የሚጠብቅ "ወኪል ድርጅ
ት" ይሆናል ማለት ነው።የህዝብ መንግስት ሲባል የዛሬን በዝባዦች በ
ሀይል ሰብሮና ከስልጣን አስወግዶ በሱ ቦታ የዛሬ ተጠቂዎች በሙሉ በ
አንድነት ተደራጅተው ጥቅማቸውን የሚጠብቁበት አዲስ ስርአት ይዘ
ረጋል ማለት ነው።እዚህ ላይ የዛሬን በዝባዦች ነጥለን ያሳየነውን ያህል
በዚህ ስርአት ውስጥ የተጨቆኑት ክፍሎች እነማን እንደሆኑ ማሳየት
ያስፈልጋል።እርግጥ ዋና ተጠቂዎች በትግሉ እስከመጨረሻ የሚገፉት
ጢሰኛ ገበሬዎችና ላብ አደሩ መሆናቸው ጥርጥር የለውም።ግን ዛሬ በ
ኢትዮጵያችን ለውጥንና እርምጃን የሚፈልጉ፣በባላባቶችና በባእድ በ
ለገንዘቦች የተጨቆኑ፣ስለዚህም ለመታገል የሚችሉና የሚደራጁ ሌሎ
ችም አሉ።ለሃገሪቱ እርምጃና ለህዝቡ ደህንነት ለመታገል እነዚህም ፀ
ረባላባትና ፀረኢምፔሪያሊስት አገር ወዳድ ሀይሎች በትግሉም ውስጥ
ሆነ በነገይቱ ህዝባዊት ኢትዮጵያ ተገቢ ቦታቸውን ማግኘት አለባቸ
ው።ስለዚህ ህዝብ ስንል ጢሰኛ ገበሬንና ላብ አደሩን ብቻ ሳይሆን በአ
ሁኑ ጊዜ በየባላገሩ ከጢሰኛው ገበሬ በማይሻል የኑሮ ደረጃ እየማቀቀ
የሚኖረውን ባለመሬት አርሶ በላና በታላላቆቹ ባላባቶችና በባእድ በዝ
በዦች ታፍኖ የቀረቀዘውን የሃገርየውን ነጋዴ፣ችጋር ከባላገር አባርት
ስራፈትነት ያንገላታቸውን የከተማ ችግረኛ፣በያለበት ተሰማርቶ የእው
ቀትን ብርሃን ለማስፋፋት በኑሮ ጠርዝ ላይ የሚባክነውን አስተማሪ፣በስ
ርአቱ ታፍኖ ለሃገሩ እንዳይሰራ የተከለከለውን ምሁር፣ለህዝብ የሚረዳ
እውቀት እንደውሃ የጠማውን አገር ወዳድ ወጣት . . . ወዘተ፣ባጭሩ ከ
ላይ የጠቀስናቸው በዝባዦችና አጫፋሪዎቻቸው በስተቀር በመላ የኢ
ትዮጵያን ህዝብ እየጨመርን ነው።
ህዝባዊው መንግስት ከላይ የዘረዘርናቸውን ልዩ ልዩ የህዝ

ብ ክፍሎች ተገቢ ጥቅም በደንብ ይጠብቃል።ለዚህም ከላይ የጠቀስና ቸውን መሰረታዊ የህዝብ ፍላጐቶች ለማርካት ግልፅና አጠቃላይ የሆነ የስራ ፕሮግራም በትግሉ ውስጥ መተለም አለበት።

የዚህ ፕሮግራም ጥና ዋና መልከቹ ከዚህ በፊት በተግሪ ስብሰባዎች ላይ ትወስተጥል።ዋናው አላማ መቸም የጊዜውን የበዝበገሮች መንግስት አስወግዶ በሱ መቃብር ላይ ከባላባት ጭቆናና ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ የተላቀቀ ህዝባዊ መንግስት ለማቋቋም መጣር ነው። ይህ ህዝባዊ መንግስት በዛሬው አገዛዝ ስር ተረግጠው የተያዙትን የህዝቡን ሰብአዊ መብቶች ያከብራል፣የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት ያቅዳል፣ይመራል፣ያቀናብራል፣እውቀትን ያስፋፋል፣ሰላምን፣አንድነትንና እኩልነትን፣በሃገሪቱ ያሰፍናል፣በነገዶችና በሃይማኖቶች መከከል ያለውን ግጭት በትክክልና በእኩልነት ይፈታል፣በፆታ መከከል ያለውን ልዩነት ይሰርዛል፣በጠቅላላው ለህዝብ ነፃነት፣እኩልነት፣አንድነት፣ሰላምና ብልፅግና ይጥራል።

ለሀገራችን እርምጃ ለህዝባችን ደህንነት የሚታየን አንድ [illegible]ገድ ይኸው በግልፅ የስራ ውጥን ላይ የተደራጀ የህዝብ ትግል ብቻ ነው።ህዝባችን ለሚያጋጥመው ችግር መፍትሄ የሚገኘው ነገድ በነገድ፣ሃይማኖት በሃይማኖት ላይ በመነሳቱ አይደለም።ተበዝባጋር በተበዝባጋር ላይ ቢነሳ ይበልጥ መከፋፈልንና ይበልጥ ጭቆናን እንጂ ነፃነትን አያተርፍም።ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ በዝባገሮች ከሚነዙት የጥላቻና የመከፋፈል ፕሮፓጋንዳ ተጠብቆ አንድነቱን እንዲያጠነክር፣ህዝባችን ትርፍ ከሌለው የእርስ በርስ እልቂት ተጠብቆ ቁጣውን፣ሀይሉን ና ጉልበቱን ለመሰረታዊ ለውጥና ለነፃነቱ ትግል እንዲያውለው ያስፈልጋል።

ህዝቡን በአንድ የትግል ግንባር ማደራጀት ፍፁም ቀላል ተግባር አይደለም።ይህ እርምጃ ብዙ ድካምና ብዙ መስዋእትነት ይጠይቃል።ነገር ግን ዝም ብሎ መቀመጥ ደግሞ ይበልጥ አሰቃቂ ነው።ህዝባችን በድህነት፣በድንቁርና፣በበሽታና በመከራ እየተሬተነ ወግ የለሽ ኑሮውን ይቀጥላል።በዚህም ቁጣ የእውር ድንብሩን ተራ በተራ እየተነሳ ሲፍጨረጨር ተራ በተራ ይደመሰሳል።ከዚህ አዘቅት ያለቆራጥ ትግል መውጣት ከንቱ ህልም ነው።ያልተደራጀ ትግል ደግሞ ሺህ ጊዜ ቆራጥ ቢሆን የድቦላ ጉዞ ነው፣ና መደናበርን መተራመስንና መደምሰስን እንጂ ድልን አያስገኝም።

የመላ ኢትዮጵያ ህዝብ የእውነተኛ ሰላም፣ነፃነትና አንድነት የተያዘው በዚህ በአንድነት በምን መሰርተው የትግል ግንባር ብቻ ነው።ሌላ ምንም መንገድ የለም።


(1) Ethiopia: an empire feeling its age. Richard West Supplement "Sunday Times" June 1964
(2) Ethiopia: A New Political History. R. Greenfield pp. 89
(3) Journal of Ethiopian Studies Vol. II No. 2 A preliminary history of the tripartite Treaty of December 13, 1906, by Harold G. Marcus.
(4) "Le Monde" 8-9 Fevrier 1970